

# ኢያሪኮ

* እያሱ ኢያሪኮን የሚሰልሉ ሁለት ሰዎች ላከ። በረዓብ ቤትም ቆዩ። የኢያሪኮ ንጉስም ስለሁለቱ ሰላዮች ወሬ ደረሰው። ስለዚህ እነርሱን ይዘው የሚመጡ ወታደሮችን ላከ። ረዓብም ሰላዮችን በጣራ ላይ ደበቀቻቸው። እንዲሁም እንዲያመልጡ ከረዳቻቸው በኋላ ቀይ ጨርቅ በቤቷ መስኮት ላይ አንጠለጠለች። ሰላዮቹም በገመድ በግንቡ ላይ ተንጠልጥለው ከወረዱ በኋላ ወደእያሱ ሄዱ። ለረዓብም እነርሱ ከተማይቱን በሚያጠፉበት ጊዜ እርሷንና ቤተሰቦቿን እንደሚያድኗት ቃል ገቡላት።

* አስራኤላውያን አሁን የመጡበት አገር ከነዓን ይባላል። ወይንም የተስፋው ምድር ተብሎም ይጠራል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ከረጅም አመታት በፊት እንደሚያወርሳቸው ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበርና ነው።

* ወደ ከነአን ምድር ከገቡ በኋላ ምድሪቱ የምታፈራውን ፍራፍሬና እህል መመገብ ጀመሩ። ከሰማይ እግዚአብሔር የሚልክላቸው መናም አቆመ።

* በኢያሪኮ አጠገብም ሰፈሩ። ኢያሪኮ በዙሪያዋ ረጅም ግንብና ትልልቅና ጠንካራ በሮች የነበሯት ከተማ ነበረች። የኢያሪኮ ነዋሪዎች ስለእስራኤላውያን ሰምተው ነበር። በዚህም ምክንያት እስራኤላውያንን እጅግ በጣም ፈሩአቸው።

* እግዚአብሔርም ከተማይቱን የሚወርሱበትን እቅድ አውጥቶ ሰጠው። ሕዝቡ ለስድስት ቀናት አንድ ጊዜ ከተማይቱን ይዞራሉ። ከእነርሱ ጋር የነበሩት ካህናትም ቀንደ መለከትን ይነፉ ነበር። ማንም አንዳች አይናገርም ነበር። እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ።

* በሰባተኛው ቀን ግን እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ። ካህናቱም ቀንደ መለከታቸውን ነፉ። ሕዝቡም ታላቅ ጩኸት ጮኹ። የኢያሪኮ ግንብ ፈረሰ። እስራኤላውያንም በቀላሉ ከተማይቱን መያዝ ቻሉ።

* በረዓብ ቤት መስኮት ላይም ቀይ ሪበን ተንጠልጥሎ ነበር። እስራኤላውያንም ለረዓብ እንደገቡላት ቃል ረዓብንና ቤተሰቧን አዳኑ። ረዓብም ከዚያ በኋላ እስራኤላዊ ባል አገባች። ወንድ ልጅም ወለዱ። ከብዙ ትውልድ በኋላም ከእርሷ ዘር አንድ ወንድ የእስራኤል ንጉስ ሆነ። ስሙም ዳዊት ይባላል። እርሱም የረዓብ የልጅ ልጅ ነው። ከዚህ በኋላም ከሌሎች ብዙ ዓመታት በኋላ ከዚሁ ቤተሰብ ሌላ ልጅ ተወለደ። ስሙም ኢየሱስ ይባላል።

ይህ የኢያሪኮ ግንብ መፍረስና ኢያሪኮ በእስራኤላውያን እጅ መውደቅ ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በመፅሐፈ እያሱ በምዕራፍ 5፡ 13-15 እና በምዕራፍ 6 ነው።

http://gardenofpraise.com